

# ሌድ (እርሳስ) ምንድነው? ከባድ ችግር የሆነው ለምንድነው?

ሌድ ለብዙ ዓመታት በቀለም ውስጥ፣ በቤንዚን ውስጥና በቧንቧ ውስጥ ይጠቀሙበት የነበረ መርዘኛ ብረት ነው። ዕድሜያቸው ከስድስት ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች በጣም አደገኛ ነው ምክንያቱም ደማቸው ውስጥ በቀላሉ ይገባል፣ አጥንታቸውና ውስጣዊ የሰውነት ክፍላቸው ውስጥ ተጠራቅሞ ይቀመጣል።

የሚላጥ እርሳስ ያለው ቀለም በትንሹም አፋቸው ውስጥ ገብቶ ቢውጡት፣ የትንሽ ልጆችን የአንጎል እድገትና ሌሎች የሰውነት የውስጥ ክፍሎች እድገት ሊጎዳ ይችላል። በእርሳስ የተመረዙ ልጆች ቋሚ የሆኑ የመማር ጉዳቶች፣ የዕድሜ ልክ የባሕርይ ችግር፣ የጆሮ ማዳመጥ ችግር፣ የእድገት መዘግየት እና ሌላም ከባድ የጤና ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል።

የኬምብሪጅ መኖሪያ ቤቶች ከእርሳስ ነጻ እንዲሆኑ የከተማው አስተዳደር ለሚያደርገው ጥረት እነዚህ ባንኮች ድጋፍ ይሰጣሉ፣ ብቁ ለሆኑ አምልካቾችም እርሳስ ማጥፊያ ብድር ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።

Cambridge Savings Bank

Cambridge Trust Company

East Cambridge Savings Bank
Connecting with customers.

ከእርሳስ ነጻ ስለሆነ መኖሪያ በይበልጥ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ
www.cambridgema.gov

EQUAL HOUSING OPPORTUNITY

የዚህ የታተመ ጽሑፍ ሥራ ድጋፍ ያገኘው በ U.S. Department of Housing and Urban Development (ከዩ ኤስ የመኖሪያና ከተማ ልማት) ጋር ባለ ስምምነት ሥር ካለ የገንዘብ እርዳታ ነው። የሥራው ግኝቶች ለሕዝቡ ይውላል። በዚህ የታተመ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኘው መረጃ ትክክልነትና ትርጉም ሙሉ በሙሉ የጸሐፊውና የአታሚው ኃላፊነት ነው። እነዚህ ትርጉሞች በግድ የመንግሥቱ አቋምን አያመለክቱም።



# ቤተሰብዎን ከእርሳስ ቀለም መመረዝ ይጠብቁ

# የማሳቹሴትስ የእርሳስ ሕግ ምንድነው?

በማሳቹሴትስ ሕግ መሠረት፣ ማንኛውም ከስድስት ዓመት በታች የሆነ ልጅ የሚኖርበት አፓርትመንት ወይም የአንድ ቤተሰብ ቤት፣ የልጁ ደም የሚያመለክተው የእርሳስ መጠን ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ፣ ቤቱ የራስ ሆነም አልሆነም ከእርሳስ መመረዝ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆን አለበት። የMassachusetts Department of Public Health Childhood Lead Poisoning Prevention Program (CLPPP) (የማሳቹሴትስ የጤና ጥበቃ የልጆች እርሳስ መመረዝ መከላከያ መርሃ ግብር) እንደሚገልጸው ከእርሳስ ነጻ ማለት "የእርሳስ ጥሰቶች ሁሉ መነሳት ወይም መሸፈን አለባቸው"። ሁሉም የእርሳስ ቀለም መነሳት ወይም መሸፈን የለበትም። እርሳሱ ከተሸፈነ በኋላ፣ አንድ ቤት "ከእርሳስ መመረዝ ደህንነቱ የተጠበቀ" ነው እንጂ "ከእርሳስ ነጻ" አይደለም።

# የመረጃ ምንጮች

## የCAMBRIDGE የጤና ጥበቃ መምሪያ

Cambridge Public Health Department

www.cambridgepublichealth.org | Lead Safe Kids (ከእርሳስ ደህንነታቸው የተጠበቁ ልጆች): 617-665-3831 (እንግሊዝኛ) 617-665-3863 (ስፓኒሽ/ፖርቹጊዝ) | 119 Windsor St., Ground Level. Cambridge, MA 02139

- "Lead-Safe Kids" ዕድሜያቸው ከ6 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ስለ እርሳስ መመረዝ ትምህርትና እርሳስን እንዴት እንደሚያጠፉ የሚያሳውቅ መርሃ ግብር ነው።
- ቤተሰቦች መርማሪ እንዲያገኙ፣ ለማገኛ የሚሆን ገንዘብ እንዲያገኙና እንዲያመለክቱ እንዲሁም ሥራውን የሚሠራ ሰውን እንዲያገኙ ይረዳል።
- የቀለም አቧራ በየቦታው የሚበታትንና ወደ ጎረቤት ግቢ የሚረጭ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ሥራ እየተሠራ ነው ተብሎ አቤቱታ ሲቀርብ ያንን ለማስቆም ጥረት ማድረግ።

## የCAMBRIDGE ሰብዓዊ መብቶ ኮሚሽን

www.cambridgema.gov/hrc | 617-349-4396 | 51 Inman Street, 2ኛ ፎቅ. . Cambridge, MA 02139

- ዕድሜያቸው ከ6 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችና ነፍሰጡር ሴቶች እርሳስ ያለው ቀለም ስላለ ቤት ሲከለከሉ የከተማ አስተዳደሩን የትክክለኛ መኖሪያ ድንጋጌ ያስከብራል።
- CHRC አቤቱታውን ይመረምራል። በነጻ። የአቤቱታ ባዩን አገር ውስጥ መኖሪያ ፈቃድ አይጠየቅም።
- አቤቱታዎች የሚከተሉትን በተመለከተ ሊሆኑ ይችላሉ:-
  - ለቤተሰብ ማከራየት መከልከል
  - አንዲት ሴት ነፍሰጡር ስትሆን ውል ማደስ መከልከል
  - እርሳስ አለ በማለት ተከራዮችን የሚያዳክም ማስታወቂያ
  - መከራየት የሚፈልጉ ሰዎችን ወደ ሌላ መኖሪያ መምራት
  - ተከራይ የእርሳስ ማስወገጃ ስለጠየቀ አጸፋ መመለስ
- አድሎ ከተገኘ መፍትሔዎች:-

  መኖሪያው ከእርሳስ ነጻ እንዲሆን ማስገደድ/የመኖሪያ አስተዳዳሪውና የቤት አሻሻጩ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ/የገንዘብ ካሳ

## የኬምብሪጅ ምርመራ አገልግሎት መምሪያ

www.cambridgema.gov/inspection | 617-349-6100 | 831 Massachusetts Avenue. Cambridge MA 02139

- O1978 ዓ.ም. በፊት የተሠራ የኪራይ ቤት ውስጥ ዕድሜያቸው ከ6 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ወይም ነፍሰጡር ሴቶች ካሉ የእርሳሱን መጠን መለኪያ ምርመራዎች ይሰጣል። የእርሳስ መጠን መለኪያ ምርመራዎች ሙሉ የእርሳስ ምርመራ እንዲደረግ ሊያደርጉ ይችላሉ።
- የተመረመሩ መኖሪያዎች ሙሉ የእርሳስ ምርመራ እንዲደረግላቸው ለ Childhood Lead Poisoning Prevention Program (CLPPP) ያስተላልፋሉ። እርምጃውን የሚያስከብሩት ከ CLPPP ጋር በመተባበር ነው።
- ከ1978 ዓ.ም. በፊት የተሠሩ ቤቶች ላይ ትክክል ያልሆኑ የእርሳስ ማስወገጃ ሥራዎች ከታዩ ለ Massachusetts Division of Occupational Safety (DOS) (የማሳቹሴትስ የሥራ ደህንነት ክፍል) ጉዳዮችን ማስተላለፍ።